# ዜና አመዝኤ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 13 ቁጥር 5 ታህሳስ 1999




## በዚህ ዕትም ውስጥ


በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ በዓይነትና በገንዘብ ከብር 65 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል
ገጽ 5

ለታህሳስ ወር ከ271 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል
ገጽ 6

ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ በቴሌቶን ዝግጅት የተሰጠውን የሕዝብ ምላሽ አደነቀ
ገጽ 6


# የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ጉብኝት በድሬደዋ /ሪፖርታዥ/

ሐምሌ 29 ቀን 1998 ዓ.ም በድሬዳዋ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ቤት ንብረታቸውን ያጡ ወገኖች በጊዜያዊ መጠለያ ሆነው የሌሎችን የዕርዳታ እጅ ጠባቂ ከሆኑ ወደ አምስት ወራት ተቆጥረዋል፡፡

እነዚህ ወገኖች ከአደጋው መከሰት ማግስት ጀምሮ ለዕለት የሚያስፈልጋቸውን ጉርስም ሆነ የመገልገያ ቁሳቁሶች ከመንግሥት ፣ ከተለያዩ የረድኤት ድርጅቶች እና እንዲሁም ከህዝቡ እያገኙ ለዘለቄታው የሚቋቋሙበትን ሁኔታም ከነዚሁ ወገኖች በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነሱን ለዘለቄታው ለማቋቋሙ ደግሞ ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚሻ ነገር ግን በጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት ሊከናወን የማይችልና ጊዜ የሚጠይቅ ሥራ በመሆኑ መንግሥት ፣ መላው የሀገሪቱ ህዝብ እና የተለያዩ የረድኤት ድርጅቶች የጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖቻችንን ለዘለቄታው መቀቋቋም እውን ለማድረግ እንቅስቃሴ የጀመሩት ከአደጋው መከሰት ማግስት ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተርና የብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሰብሳቢ በአቶ ሲሞን መቻለ የተመራው ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ፣ የሃይማኖት መሪዎችንና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን ያካተተው ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ታህሳስ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በድሬዳዋ ያደረገው ጉብኝት ዓላማም የዚህኑ የጎርፉ ተጎጂ ወገኖችን ለዘለቄታው የማቋቋም ሥራ ጅምሮችን በቦታው ተገኝቶ ለማየት እና በጊዜያዊ መጠለያ ያሉትን ተጎጂ ወገኖች በመጎብኘት በቀጣይ ስለሚወሰደው እርምጃ ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላትና ከተጎጂዎች ጋር ለመወያየት ነበር፡፡ በዕለቱ የድሬዳዋ መስተዳድር



ከንቲባ አቶ አብዱልአዚዝ መሀመድ ለኮሚቴው አባላት እንደገለጹት በጎርፉ አደጋ ቤት ንብረታቸውን አጥተው ተፈናቃይ ከሆኑት አጠቃላይ 9 ሺህ 956 ወገኖች ውስጥ 5 ሺህ 524 ሰዎች በተዘጋጀላቸው ጊዜያው መጠለያ የሚገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 4 ሺህ 432 ሰዎች ደግሞ በየዘመድ ቤት ተጠግተው ይገኛሉ፡፡ እንደከንቲባው ገለጻ በጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙት ወገኖችም ሆኑ በየዘመዶቻቸው ቤት ተጠግተው ያሉቱ አደጋው ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ


በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፡ www.dppc.gov.et



ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተገዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

ወርሃዊ ራሽን እያገኙ ናቸው።

ለጎርፉ ተፈናቃይ ወገኖች ወርሀዊ ቀለብ ከማቅረብ ጎን ለጎን ተጎጂዎቹን ለዘለቄታው ለማቋቋም እየተደረጉ ካሉ እንቅስቃሴዎች አንዱና ዋንኛው የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣የሀይማኖት ተቋማት ፣ የግል ድርጅቶች ፣ ግለሠቦች ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወገኖች ፣ በአጠቃላይ መላው ህዝብ "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚል መርህ የሚለግሠውና በብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው አማካይነት የሚሰበሰበው ገንዘብ ሲሆን



ሌላው ደግሞ በዚሁ ኮሚቴ አስተባባሪነት አንዳንድ የግል እና የረድኤት ድርጅቶች ለተጎጂዎቹ ቤት ሠርተው ለመስጠት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው።



አያት የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ድርጅት ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች ለ26 አባወራ የሚሆኑ ቤቶችን ገንብቶ ታህሳስ 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው በማስረከብ የመጀመሪያው ሆኗል።

በዚህ መሰል እንቅስቃሴ በመሳተፍ ቀዳሚነቱን የወሰደው እና በውጤቱም በአርአያነት ለመጠቀስ የበቃው የአያት የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ድርጅት ነው። አያት የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ድርጅት ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች ለ26 አባወራ የሚሆኑ ቤቶችን ገንብቶ ታህሳስ 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው በማስረከብ የመጀመሪያው ሆኗል።

የድርጅቱ የንግድ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ፍቃዱ በቀለ በርክክቡ ወቅት እንደገለጹት እያንዳንዳቸው 1 መኝታ ቤት 1 ሳሎንና የመመገቢያ ቤት ፣ 1ዕቃ ቤት እና የየራሳቸው መፀዳጃ ቤት ያላቸውን 26 ቤቶች ሠርተው ለማጠናቀቅ የወሰደባቸው ጊዜ ሦስት ወራት ብቻ ነው። ለእነዚህ ቤቶች ግንባታ ድርጅቱ ብር 1 ሚሊዮን 600 ሺህ ማውጣቱንም አቶ ፈቃዱ ተናግረዋል። ድርጅታቸውን ለዚህ ተግባር ያነሳሳው ምን እንደሆነ አቶ ፈቃዱ ሲናገሩም የአደጋው ተጎጂዎች በጎርፉ ከተነጠቋቸው ንብረቶች ዋንኛው ቤት በመሆኑ እና ቤትን መገንባት ሞያችንና ድርጅታችን የተሠማራበት የሥራ ዘርፍ በመሆኑ በሙያችንና በተሠማራንበት የሥራ ዘርፍ ወገኖቻችንን እንርዳ ከሚል ነው ብለዋል።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር እና የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሲሞን መቻለ የቤቶቹን ቁልፎች ከተረከቡ በኋላ አያት የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ድርጅት ከዚህ ቀደም ለተመሳሳይ ተግባር 100 ሺህ ብር መለገሱን ጠቅሰው አደጋው በተከሰተ ማግስት ቤቶችን ገንብቶ ለተፈናቃዮች ለመስጠት በገባው ቃል መሠረት ቃሉን ጠብቆ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እነዚህን ቤቶች ሠርቶ ለተፈናቃይ ወገኖች ማበርከቱ በእጅጉ የሚያስመሰግነውና በአርአያነት የሚያስጠ ቅሰው ነው ብለዋል። ዋና ዳይሬክተሩ በራሳቸው ፣ በብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው እና በተጎጂ ወገኖች ስም ድርጅቱን አመስግነው የቤቶቹን ቁልፎች ለድሬደዋ



ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ለአቶ አብዱልአዚዝ መሀመድ አስረክበዋል።

ከንቲባ አብዱልአዚዝ መሀመድ እና ሌሎች የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ አባላትም አያት የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ድርጅት ለወገን ጥሪ ላሳየው ፈጥኖ ደራሽነት

አድናቆትና ምስጋናቸውን ገልፀው ሌሎች መሰል ድርጅቶችም ይኸንኑ አርአያ እንዲከተሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው አባላት በጎርፍ አደጋ ተፈናቃይ ለሆኑት ወገኖች በሐረርጌ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እየተገነቡ ያሉ ቤቶችንም ተመልክተዋል፡፡ በጉብኝቱ ወቅት እንደተገለጸው ቤተክርስቲያኒቷ የምታስገነባቸው 200 ቤቶች እያንዳንዳቸው ሳሎንና አንድ መኝታ ክፍል እንዲሁም መፀዳጃ ቤት ይኖራቸዋል፡፡ የቤቶቹ ግንባታ ከሦስት ወር እስከ ሦስት ወር ተኩል በሚሆን ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚታሰብም ተጠቅሷል፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ ለነዚህ ቤቶች ግንባታ 6 ሚሊዮን ብር ወጭ እንደምታደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ቤተክርስቲያኒቷ የምታስገነባቸው 200 ቤቶች እያንዳንዳቸው ሳሎንና አንድ መኝታ ክፍል እንዲሁም መፀዳጃ ቤት ይኖራቸዋል፡፡ የቤቶቹ ግንባታ ከሦስት ወር እስከ ሦስት ወር ተኩል በሚሆን ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚታሰብም ተጠቅሷል፡፡



የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፣ አባላት እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አብዱልአዚዝ መሀመድ በጋራ እንደገለጹት የሐረርጌ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አደጋው ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ለተጎጂዎቹ ቀለብና ቁሳቁስ በማቅረብ ከምታደርገው የቅርብ ድጋፍ በተጨማሪ ቤቶችን ገንብታ ለመስጠት የጀመረችው እንቅስቃሴ የሚያኮራ ነው፡፡ የቤቶቹ ግንባታ በተባለው ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ከመጠለያ ኑሮ ለመውጣት በተስፋ ለሚጠባበቁት ወገኖች እንደሚደርስ እምነታችን ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት ለጎርፉ ተፈናቃዮች የሚሆኑ ቤቶችን ለመገንባት ቦታ የመከለል እና ግንባታውን የሚያካሔዱ ሥራ ተቋራጮችን መምረጥ የመሳሰሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አጠናቆ ግንባታ ለመጀመር ዝግጅት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህ ግንባታ ሁለት ለግንባታ የተከለሉ ቦታዎች የተመረጡ ሲሆን በአንደኛው ለግንባታ በተከለለው ቦታ ላይም እያንዳንዳቸው 15 አባወራ የሚይዙ አምስት የኮንዶሚኒየም ህንፃዎች ይገነባሉ፡፡ ለዚህ ግንባታ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ለጎርፍ ተጎጂዎች የለገሡትና በአስተዳዳሩ የባንክ ሒሳብ የሚገኝ ብር 10 ሚሊዮን እንዲሁም ብር 5 ሚሊዮን የሚያወጡ የግንባታ ቁሳቁሶች በድምሩ ብር 15 ሚሊዮን ያህል ወጭ እንደሚደረግ ለግንባታው የተመረጠው ቦታ በተጎበኘበት ጊዜ ከተደረገው ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለመሠል ግንባታ በተመረጠው ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ለ330 አባወራ የሚሆኑ ቁጠባ ቤቶች ይሠራሉ፡፡ ለነዚህ ቤቶች ግንባታ ደግሞ ክርስቲያን ችልድረን ፈንድ /ሲ.ኤች.ኤፍ/ ከተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የተገኘ ብር 2 ሚሊዮን ፣ ከመንግሥት ብር 8 ሚለዮን በድምሩ ብር 10 ሚሊዮን ወጭ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡ በሁለቱም ቦታዎች ላይ የሚሠሩት ቤቶች ግንባታ መጭው ክረምት ከመግባቱ በፊት እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፡፡

የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ አባላቱ በመጠለያ ተገቃተው በአደጋው ተፈናቃይ የሆኑትን ወገኖችም ጎብኝተዋል ፣



ተጎጂዎቹ የሚኖሩባቸው ድንኳኖች ለቀን ሙቀትም ሆነ ለሌሊት ብርድ የማይመቹ ፣ በርካታ ህዝብ በዚህ ዓይነት በአንድ ላይ መኖሩ በተለይ ለህፃናቶች ጤና ጥሩ እንዳልሆነና በዚህ ሁኔታ ከቆዩም ያለፈው ችግር ድጋሚ ሊገጥማቸው እንደሚችል ስጋት እንዳለባቸው ገልፀው መንግሥትና ህዝቡ ለቤቶች ሥራ ትኩረት ሠጥተው በአፋጣኝ ከዚህ እንዲያወጡን እንማፀናለን ብለዋል::



ከንቲባ አብዲልእዚዝ መሀመድ እንደገለጹት ተጎጂዎቹን አጠቃሎ ከመጠ ለያ ለማውጣት የሚያስፈልጉት 1 ሺህ 600 ቤቶች ናቸው:: ከዚህ ውስጥ እስካሁን ግንባታቸው የተጠናቀቀ እና በጅምር ያሉ 600 ቤቶች ሲሆኑ ፣ የ1000 ቤቶችን ግንባታ ሥራ ለማካሄድ ከ38 ሚሊየን ብር በላይ ያስፈልጋል::

አነጋግረዋል:: በዚሁ ጊዜ የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎቹ እንደተናገሩት በወርሃዊ ቀለብ አቅርቦትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ድጋፍ በኩል ችግር እንደሌለባቸውና አሁን ዋነኛውና አንገብጋቢው ችግራቸው አንገታቸውን የሚያስገቡበት፣ ልጆቻቸውን



የሚሠበስቡበትና ለዘለቄታው የሚኖሩበት ቤት ነው:: ተጎጂዎቹ የሚኖሩባቸው ድንኳኖች ለቀን ሙቀትም ሆነ ለሌሊት ብርድ የማይመቹ ፣ በርካታ ህዝብ በዚህ ዓይነት በአንድ ላይ መኖሩ በተለይ ለህፃናቶች ጤና ጥሩ እንዳልሆነና በዚህ ሁኔታ ከቆዩም ያለፈው ችግር ድጋሚ ሊገጥማቸው እንደሚችል ስጋት እንዳለባቸው ገልፀው መንግሥትና ህዝቡ ለቤቶች ሥራ ትኩረት ሠጥተው በአፋጣኝ ከዚህ እንዲያወጡን እንማፀናለን ብለዋል::

ከጉብኝቱ በኋላ በመስተዳድሩ ም/ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተደረገው የማጠ ቃለያ ውይይት ትኩረት የተሰጠው



ተጎጂዎቹን ወደዘላቂ ኑሮአቸው እንዲመለሱ በማስቻል ረገድ ዋንኛ በሆነው በአፋጣኝ ከመጠለያ የማውጣት ሥራ ነው:: በዚሁ ውይይት ላይ ከንቲባ አብዲልእዚዝ መሀመድ እንደገለጹት ተጎጂዎቹን አጠ ቃሎ ከመጠለያ ለማውጣት የሚያስፈልጉት 1 ሺህ 600 ቤቶች ናቸው:: ከዚህ ውስጥ እስካሁን ግንባታቸው የተጠናቀቀ እና በጅምር ያሉ 600 ቤቶች ሲሆኑ ፣ የ1000 ቤቶችን ግንባታ ሥራ ለማካሄድ ከ38 ሚሊየን ብር በላይ ያስፈልጋል::

መጭውን የክረምት ወቅት በመጠለያ ውስጥ ማሳለፉ በተጎጂዎቹ ላይ ያሳደረውን ስጋት እንደሚጋሩት የተናገሩት ከንቲባ አብዱልአዚዝ መንግሥትና ህዝብ እስካሁን ስናደርገው እንደቆየነው ተጎጂዎችን ለመታደግ የምናደርገውን ጥረት በማጠናከር ለግንባታው የሚያስፈልገውን ገንዘብ በማሰባሰብ መጪው ክረምት ወቅት ከመግባቱ በፊት ተጎጂዎችን ከመጠለያ ለማውጣት መረባረብ ይኖርብናል ብለዋል::

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር እና የዕርዳታ አሰባሳቢ ብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሲሞን መቻል በበኩላቸው የሚቻለውን ሁሉ አድርጎ ተጎጂዎቹን ከመጪው የክረምት ወቅት በፊት ከመጠለያ የማውጣቱን ሀሳብ እሳቸውም ሆኑ የኮሚቴው አባላት አጥብቀው እንደሚያምኑበት አመልክተው በብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው አማካይነት እስካሁን ከህብረተሰቡ ከተሰበሰበውና በእጅ ካለው ገንዘብ ውስጥ ለድሬዳዋ የሚደርሰው መጠን በቅርቡ እንደሚለቀቅ አመልክተዋል:: በመቀጠልም ይኸ ገንዘብ በቀጣይነት መገንባት ያለባቸውን ቤቶች ለማስጨረስ ባይችል እንኳን ለማስጀመር የሚያስችል በመሆኑ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ባፋጣኝ ተሟልተው ግንባታው እንዲጀመር አሳስበዋል:: ግንባታዎቹን እንደተባለው ከመጪው ክረምት በፊት ለማጠናቀቅ ህብረተሰቡ ለመለገስ ቃል የገባውን በወቅቱ ገቢ በማድረግም ሆነ ተጨማሪ ዕርዳታ በመለገስ የተለመደ የወገናዊነት ድጋፉን አጠ ናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል::

በመጨረሻም ብሔራዊ ኮሚቴው በድሬዳዋ የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴን ለመመልከት ያደረገው ጉብኝት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እንደማይሆንና በተመሳሳይም

፤ባለፈው ክረምት ወቅት የጎርፉ አደጋ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ያሉ ተጎጂዎችን ለማቋቋም የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በቦታው ተገኝቶ በመጎብኘት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ በውይይቱ ላይ ተመልክቷል።

## በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ በዓይነትና በገንዘብ ከብር 65 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ ከሀገር ውስጥ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣ የልማት ድርጅቶች ፣ የክልል መንግሥታት ፣ ማህበራት ፣ ዕድሮች ፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ግለሰቦች ፣ ከሀገር ውጭ ደግሞ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ፣ የውጭ መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 65 ሚሊዮን 243 ሺህ ከ85 ሳንቲም ለግሰዋል።



ከዚሁ እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ከተለገሠው ጠቅላላ ዕርዳታ ውስጥ ብር 49 ሚሊዮን 297 ሺህ ከ68 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብ የተለገሠ ሲሆን ቀሪው ብር 15 ሚሊዮን 945 ሺህ 325 ከ44 ሳንቲም ደግሞ በዓይነት የተለገሠ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የዕርዳታ ማሰባሰብ ቡድን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን በተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የሚለገሠው ዕርዳታ በማዕከል እና በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል አማካይነት የሚሰባሰብ መሆኑም ይታወቃል።

በዚሁ መሠረት እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1999 ዓ.ም በጥሬ ገንዘብ ከተለገሰው ጠቅላላ ብር 49 ሚሊዮን 297 ሰህ 754 ከ68 ሳንቲም ውስጥ ብር 40 ሚሊዮን 096 ሺህ 210 በማዕከል ቀሪው ብር 9 ሚሊዮን 201 ሺህ 549 ከ68 ሳንቲም ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳዳር ካውስል የተሰበሰበ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በተመሳሳይ እስከተጠቀሰው ጊዜ ድረስ በዓይነት ከተለገሠው ጠቅላላ ብር 15 ሚሊዮን 945 ሺህ 325 ከ44 ሳንቲም ውስጥ ብር 7 ሚሊዮን 817 ሺህ 387 የሚሆነው በማዕከል ቀሪው ብር 8 ሚዮን 127 ሺህ 938 ከ44 ሳንቲም ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳዳር ካውስል የተሰበሰበ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ ከሀገር ውስጥ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣ የልማት ድርጅቶች ፣ የክልል መንግሥታት ፣ ማህበራት ፣ ዕድሮች ፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ግለሰቦች ፣ ከሀገር ውጭ ደግሞ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ፣ የውጭ መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 65 ሚሊዮን 243 ሺህ ከ85 ሳንቲም ለግሰዋል።

## ለታህሳስ ወር ከ271 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል

በተለያዩ ክልሎች በተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለታህሣሥ ወር በጠቅላላው 272 ሺህ 089 ኩንታል እህል የተመደበ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ለወሩ የተመደበው የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ሙሉ በሙሉ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የተመደበው መሆኑንም ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል።

በታህሣሥ ወር የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ የተመደበው ለሱማሌና አማራ ክልሎች ሲሆን ፣ ለወሩ ከተመደበው ጠቅላላ 272 ሺህ 089 ኩንታል ውስጥ 271 ሺህ 208 ኩንታል ለሱማሌ ቀሪው 881 ኩንታል ደግሞ ለአማራ ክልል የተመደበ ነው።

ለሱማሌ ክልል ከተመደበው ጠቅላላ 271 ሺህ 208 ኩንታል ውስጥ 41 ሺህ 140 ኩንታል ለጎርፍ ተጎጂዎች ቀሪው 230 ሺህ 068 ኩንታል ደግሞ በአየር መዛባት ሳቢያ የምግብ እጥረት ላጋጠማቸውና የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የክልሉ ነዋሪዎች የተመደበ መሆኑ ታውቋል።

## ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ በቴሌቶን ዝግጅት የተሰጠውን የሕዝብ ምላሽ አደነቀ

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ ወዳጆች ህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በሸራተን አዲስ በተካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ዝግጅት ላይ የሰጡት ምላሽ እጅግ የሚያኮራና የሚደነቅ መሆኑን ገለፀ።

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ ወዳጆች ህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በሸራተን አዲስ በተካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ዝግጅት ላይ የሰጡት ምላሽ እጅግ የሚያኮራና የሚደነቅ መሆኑን ገለፀ።

ኮሚቴው ታህሳስ 5 ቀን 1999 ዓ.ም ባካሄደው 8ኛ መደበኛ ስብሰባው የቴሌቶን ዝግጅቱን ሂደትና ሌሎች የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች መርሀ ግብሮችን በገመገመበት ወቅት እንዳመለከተው በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የቃል ኪዳን ቅጽ በመሙላት ከመላክ ጀምሮ በቀጥታ ስልክ መስመሮች የጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖችን ለመደገፍ ያደረጉት ርብርብ “ለወገን ደራሽ ወገን” መሆኑን በተግባር ያስመሰከሩበት ነው ብሏል።

እንደብሔራዊ ኮሚቴው ግምገማ መንግሥትና ተባባሪዎቹ በመላው አገሪቱ በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን ከ674 ሺህ በላይ ወገኖችና ከነዚህም ውስጥ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን 242 ሺህ ያህል ተጎጂዎች የዕለት ዕርዳታ ከማቅረቡ ጎን ለጎን መልሶ ለማቋቋም በመደረግ ላይ ላለው ጥረት በቴሌቶኑ የአውሮጠ ህብረት በሁለትዮሽ ስምምነት የለገሠውን ሳይጨምር በሀገር ውስጥ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ፣ ከውጭ ፣ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የተገኘው በገንዘብና በዓይነት ቃል የተገባው ብር 30 ሚሊዮን ምላሽ ይበልጥ ያጎለብተዋል።

የኮሚቴው አባላት በዚሁ መደበኛ ስብሰባ ላይ እንዳስታወቁት በቴሌቶኑ ዕለትና ከዚያን ወዲህ የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም ከህፃን እስከ አዛውንት ፣ ከግለሰብ እስከ የንግድ ድርጅቶችና ተቋማት በአንድ ቃልም ሁሉም ያለውን ለወገኑ ለማካፈል በገባው ቃል የወገን አለኝታነቱንና መከታነቱን አስመስክሯል። ከዚህም በላይ ደግሞ ሰብዓዊ ድጋፍ በአገርና በክልል ብቻ የማይወሰን ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ያለው መሆኑንም የቴሌቶን ዝግጅቱ ሌላው

ያረጋገጠው እውነታ ሆኖ አግኝቶታል ብለዋል።

የጎርፍ ተጎጂ ወገኖችን መልሶ የማቋቋሙ ሥራ ለነገ የማይባል ጊዜ የማይሰጥ ተግባር ነው ያለው ብሔራዊ ኮሚቴው ከዚህ እውነታ በመነሳትም በቃላቸው መሠረት ቃል የገቡትን ገንዘብ ገቢ ላደረጉ ለጋሾች በተረጂ ወገኖች ሥም ከፍተኛ ምስጋና አቅርቧል። በተመሳሳይም ቃል የገቡ ለጋሽ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለዚሁ ለተቀደሰ ዓላማ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚያደርጉበት ወይም የብሔራዊ ኮሚቴው ጽ/ቤት በሚገቃበት በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ይፋ የዕርዳታ ርክክብ ኘሮግራም ተይዞላቸው የሚያስረክቡበት ሁኔታም መመቻቸቱን አስታውቋል። ተጎጂ ወገኖችን መልሶ በማቋቋም ወደወትሮ ኑሮአቸው እንዲመለሱ ለማደረግ ለተጀመረው እንቅስቃሴ መፋጠን ቃል የገቡ ወገኖች ፈጣን ምላሽ ሁነኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ያመለከተው ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት የወገን ተቆርቋሪነትንና አለቃታነትን ዳግም እንዲያረጋግጡ አሳስቧል።